በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 3


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ


**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com



***<u>ቦታ፡</u>*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ጥር ፲፯ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.**

# የዳ ቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 3



# የዳቬንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 3

## ምዕራፍ ሁለት

### የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት

- አስቀድሞ እንደ ተገለጸው ዳን ብራውን በቅዱስ መጽሐፍ ላይ ያለው ክሕደት በርካታ ወደ ሆኑ ሥነ መለኮታዊ ስሕተቶች መርቶታል:: ከሁሉም በላይ ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነትና የእግዚአብሔር ልጅነት ይክዳል::
- «በአብዛኛው አባቶቻችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማሩን ትምህርት ስሕተት ነው::» *የዳ ቪንቺ ኮድ፤ ገጽ 235*
- «ኢየሱስ በተከታዮቹ እንደ ነቢይ፤ ብርታት ወይም ኃይል እንደ ነበረው ሟች በስባሽ እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ የሚቆጠር አልነበረም::» *የዳ ቪንቺ ኮድ ፤ ገጽ 233*
- «ኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር ልጅ በማለት የማንገሥ፣ የማወጅ ሥራ በግልጽ የተደነገገውና ድምፅም የተሰጠበት በኒቃያ ጉባኤ ነው:: በድምፅ አሰጣጡም ሒደት በደገፉትም ሆነ በተቃወሙት በኩል የነበረው ልዮነት እጅግ በጣም የተቀራረበ ነበር::» *የዳ ቪንቺ ኮድ ፤ገጽ 233*
- በዚህ ክስ ውስጥ የምናገኘው በልብ ወለድ ውስጥ የተፈጠረን አዲስ ታሪክ ነው:: የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት በተመለከተ ተገቢ የሆነው ትምህርት ቀድሞም ነበረ:: የኒቂያ ጉባኤም የባሕርይ አምላክነቱን ለመጀመሪያ ጊዜ ለማሳወቅ አልተደረገም:: ጉባኤው የተደረገው የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት የካደ አርዮስን ለማውገዝ ነው::
- በኒቂያ ጉባኤ በተደረገው በሃይማኖት ምስክርነት ጸሎትም ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የነበረውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት የሚያረጋግጥ ነው:: ያ ትምህርተ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን የኖረችበት፤ በቅዱሳት መጻሕፍቷና በቅዳሴዎቿ ሁሉ የተገለጸ ነው::
- በተጨማሪም ከዳን ብራውን አገላለጽ በተለየ መልኩ ሃይማኖታቸው የጸና ምግባራቸው የቀና የጉባኤው አባላት የሆኑ 318ቱ አባቶች የቀረበውን የሃይማኖት ምስክርነት በአንድ ልብ በአንድ ቃል ተቀብለዋል::

# የዳቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 3

## የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት

- ጌታችን ዳን ብራውን እንደ ተናገረው ብርቱና ታላቅ ሰው ብቻ አልነበረም:: «የእግዚአ ብሔር ልጅ» ***ሉቃስ 1:35*** «በሥጋ የተገለጠም አምላክ» ***1ኛ ጢሞ 3:16*** ነው እንጂ::
- ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ መጀመሪያ እንደ ጻፈው ጌታችን ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቃል ነው:: «በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ::» ***ዮሐ 1:1***
- በራእየ ዮሐንስም «የእግዚአብሔር ቃል» ተብሏል። ***ራእይ 19:13::*** ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት፤ ድኅረ ዓለምም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከእመቤታችን ተወለደ::
- መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም «...መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል:: የልዑል ኃይል ይጸልልሻል:: ስለዚህ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል» ***ሉቃስ 1:35-36*** ብሎ ለእመቤታችን እንዳበሠራት::
- ጌታችን ለአይሁድ እንደ ተናገረው የመጣው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው:: «እግዚአብሔርስ አባታችሁ ከሆነ በወደዳችሁኝ ነበር፤ እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፤ እርሱ ላከኝ እንጂ ከራሴ አልመጣሁም::» ***ዮሐ 8:42::*** ለደቀመዛሙርቱ «ከእግዚአብሔር እንደመጣሁ ስላመናችሁ አብ ቺርሱ ራሱ ይወዳችኋል» ብሎአቸዋል:: ***ዮሐ 16:27::***
- የአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኒቂያ ጉባኤም ሆነ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት እንደ አዲስ ማስተዋወቅ ዓላማቸው አልነበረም:: የባሕርይ አምላክነቱ (መለኮታዊነቱ) ጌታችን ራሱ በሥጋ ከተገለጠበት ጊዜ አንስቶ በባሕርይ አባቱ በአብ፤ በባሕርይ ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ እና በሌሎችም የተለያዩ መንገዶች ተገልጧል::
- እግዚአብሔር አብ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ:- «የምወደህ ልጄ አንተ ነህ ፤ በአንተ ደስ ይለኛል::» ብሎአል:: ***ማርቆስ 1:11::*** በደብረ ታቦርም ይህንኑ በመሰለ መንገድ «የምወደው ልጄ» ብሎ ገልጧል:: ***ማቴ 17:5*** ፤ ***ማር 9:7***፤ ***ካል ጴጥ 1:15-18***

# የዳቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 3

## የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት

- የጌታችንን የእጁን ተአምራት ያዩ የቃሉን ትምህርት የሰሙ ደቀመዛሙርትና ሌሎች ምስክሮች እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብለዋል:: ዳን ብራውን እንደ ጻፈው «ተራ ሰው ነው» አላሉም::
- ጌታችን ደቀመዛሙርቱን:- «እናንተስ ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው:: ስምዖን ጴጥሮስ:- አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ አለው::» ጌታችንም መልሶ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፤ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና አንተ ብፁዕ ነህ::» አለው:: ***<u>ማቴዎስ 16:15-17</u>***
- ከዮሐንስ ወንጌል አስቀድመው የተጻፉ ሦስቱም ወንጌላት:- ማቴዎስ፤ ማርቆስና ሉቃስ የሚገልጹትም ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አባቱ የአብ የባሕርይ ልጅ መሆኑን ነው:: ቅዱስ ማቴዎስ ነቢዮ ኢሳያስን በመጥቀስ:- «እነሆ ድንግል ትጸንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች ፤ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል:: ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለት ነው::» ብሎ ጽፏል:: ***<u>ማቴ 1:23፤ ኢሳ 7:14::</u>*** ቅዱስ ማርቆስም በወንጌሉ:- «የእግዚአብሔር ልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ...» ***<u>ማር 1:1</u>*** ያለ ሲሆን ቅዱስ ሉቃስ «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል::» በማለት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለእመቤታችን የተናገረውን ጽፎአል:: ***<u>ሉቃስ 1፤35::</u>***
- ***<u>ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው::</u>*** «አብ ልፈጽመው የሰጠኝ ሥራ ይህ የማደርገው ሥራ እንደ ላከኝ ይመሰክራል:: እኔ የአባቴን ሥራ ባላደርግ አትመኑኝ፤ ባደርገው ግን እኔንስ እንኳ ባታምኑ አብ በእኔ እንደ ሆነ እኔም በአብ እንደ ሆንኩ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ::» እያለም በመዋዕለ ሥጋዌው አስተምሯል:: ***<u>ዮሐ 5:36፤ ዮሐ 10፤37-38</u>***
- የመጽሐፍ ቅዱስን እውነታ የማይቀበሉ ወገኖችም እንኳን ቢሆኑ ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ ከሞተ፣ በትንሣኤውም ሞትን ድል አድርጎ ከተነሣና ካረገ ከ20 ዓመት በኋላ ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን በሮማ ዘመን ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን መጻፉን ማመናቸው ለጌታችን የባሕርይ አምላክነት ምስክር ነው: ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ የተመሠረተች ናትና:: እነዚህ መልእክታት በመጀመሪው መቶ ክፍለ ዘመን በነበሩ አብያተ ክርስቲናት ተሰራጭተው ተቀባይነት ነበራቸው::

# የዳቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 3

## የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት

- ከ40-60 ዓ.ም. በተጻፉ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ጌታችን የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ተገልጧል:: «... ስለ እኔ ራሱን በሰጠ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው::» ***ገላ 2:20::*** «ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን::» ***ቀዳ ቆሮ 8:6::***
- የኋለኞቹም የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ጌታችንን:- «የማይታየው አምላክ መልክ» ይሉታል:: «እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም::» ይላል:: ***ፊልጵስዮስ 2:6*** «እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው:: የሚቆዩትና የማይቆዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋል::»***ቈላ 1:15-16::***
- በምልዓት የሚኖር እግዚአብሔር በገሃድ እየታየ የቆየው በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በሥጋ በተገለጠ ጊዜ ነው:: «በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራል::» ቆላስያስ 2:19:: ***ቈላ 2:19::*** «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድስ እንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው::» ***ዮሐንስ 1:18::*** እንዲሁም ጌታችን «እኔን ያየ አብን አይቶአል::» በማለት ለፊልጶስ አስረድቶታል::
- የጌታችን የባሕርይ አምላክነት አጽንቶ የሚያስተምረው የዮሐንስ ወንጌል ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን መጠናቀቅ በፊት የተጻፈ መሆኑንም አስቀድሞ እንደገለጸው በግብጽ የተገኘ መረጃ አረጋግጧል:: በመጀመሪያውም መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩት ክርስቲያኖች በጌታችን የባሕርይ አምላክነት ማመናቸውን በክርስትናው ላይ በተቃውሞ የተጻፉ ጽሑፎች አረጋግጠዋል::
- ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የነበሩ ክርስቲያኖች ሥጋ ስለ ለበሰው አምላካችን ምስክር በመሆን ታስረው በሰማዕትነት አልፈዋል:: ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ማመናችን በጣም በቅርብ የተፈጠረ እንግዳ ትምህርት ከሆነ ቅዱስ እስጢፋኖስ፣ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ እና ሌሎችም በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመንና ከዚያም በኋላ ባሉት ዘመናት የነበሩት ቅዱሳን ሁሉ ስለምን በስሙ አምነው በሰማዕት ሆነው አለፉ?

# <u>የዳቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 3</u>

**የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት**

- ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ከምንሰጠው ምስክርነት በተጨማሪ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በአጠቃላይ *ሥጋ* መልበሱን፤ ሰው መሆኑን፤ ሰውን ማክበሩን አጥብቀው ያስተምራሉ። ***<u>ፊልጵ 2:7፤ ዕብ 2:17፤ ሉቃ 2:52።</u>***
- የቅዱስ ሉቃስና የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌላት ስለ ጌታችን ሰው መሆን ከሚገልጹት በተጨማሪ ጌታችን በሥጋ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን፤ በስምንተኛውም ቀን መገረዙን፤ እንደ አይሁድም ሕግ በ40ኛው ቀን ወደ ቤተ መቅደስ መሄዱን አስረግጠው ያስረዳሉ።
- በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስ በተዋሕዶ የባሕርይ አምላክ ነው ብለው በማመናቸው የሚዘነዘርባቸው ነቀፋ ብርቱ ነበር። ዳን ብራውን የግኖስቲኮች የሐሰት ጽሑፎችና በአጠቃላይ ጌታችን ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን አለመቀበላቸውን ፈጽሞ የተረዳ አይመስልም። ይኸም ማለት እርሱ ስለ ሐሰተኛ ጽሑፎቹ ከሚቀበለው ወይም ከተረዳው ፈጽሞ የተለየ ነው።
- ቅዱስ ዮሐንስ በመጀመሪያው መልእክቱ በወቅቱ ኢየሱስ ክርስቶስ *ሥግው* ቃል መኾኑን ከማመን የራቁ ወገኞች ስለነበሩ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ መምጣቱን ጽፏል። ***<u>1ኛ ዮሐ 4:2-3</u>***
- ቅዱስ ጳውሎስ «ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ይገባዋል» ብሎ ከመናገር ወደ ኋላ አላለም። ***<u>ቀዳ ጢሞ 2:5</u>*** ከዚህ በላይ እንደ ተገለጸው ቅዱስ መጽሐፍ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ፤ ከኃጢአትም ብቻ በቀር ሰው መሆኑን በአንድነት ያስተምራሉ።

# የዳቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 3

## የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት

- በተጨማሪም ታላቁ ቆስጠንጢኖስ ከነበረበት ከ200 ዓመት ቀደም ብሎ በሐዲስ ኪዳን የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት የሚገጹ ትምህርቶች በተደጋጋሚ ተጽፈዋል፡፡
- «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ... እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋቸውንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው፡፡ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡» ***ማቴ 28:18-20፡፡***
- «... ኢየሱስም እምነቆቸውን አይቶ ሽባውን አንተ ልጅ ኃጢአትህ ተሰርዮልሃል አለው... ከቆሙትም ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአትን ሊያስተስረይ ማን ይችላል? ብለው አሰቡ...» ***ማር 2:5-7*** ፤ ***ሉቃስ 5:21፡፡*** «መተላለፍህን ... የምደመስስ እኔ ነኝ ኃጢአትህንም አላስብም፡፡» ***ኢሳይያስ 43:25፡፡***
- «እኔ እንደሆንሁ እናንተ ትላላችሁ፡፡» ***ሉቃስ 22:70፡፡***
- «ሰዎች ሁሉ አብን እንደ ሚያደብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድስ እንኳን አይፈርድም፡፡» ***ዮሐ 17:5፡፡***
- «ቶማስም ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት፡፡» ***ዮሐ 20:28፡፡***
- «እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤፡፡» ***ቲቶ 2:13፡፡***
- «አምላክ ሆይ፤ ዙፋንህ ለዘለዓለም ይኖራል፡፡» ***ዕብ 1:18፤ ይሁዳ 25፡፡***
- «ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ሕያው ነኝ፡፡» ***ራእይ 1:17-18፡፡***

# የዳቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 3

## ምዕራፍ ሦስት

### የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መዋዕለ ሥጋዌ

- የጌታችንን መዋዕለ ሥጋዌ አሰመልክቶ ዳን ብራውን ነቅፎ አጠይፎ የጻፋቸው ነገሮች አሉ:: ይኸውም የባሕርይ አምላክነቱን በተመለከተ ከተናገረው ክሕደት ጋር የተመሳሰለ ነው:: ጸሐፊው መዋዕለ ሥጋዌውን በተመለከተ ከእውነት በራቀ መልኩ ኃጢአት የሌለበት እርሱን ክብር ይግባውና ከ«ጋብቻ» ጋር አያይዞ በሚከተለው መልክ አቃሎ አቅርቦቆል::
- «ኢየሱስ ክርስቶስን አስመልክቶ እኛ ያላገባ አድርገን ከመጽሐፍ ቅዱስ አገኘን ብለን ከምናምነው በተሻለ መልኩ ያገባ አድርገን መረዳቱ የበለጠ ትርጉም ይሰጣል::» ***የዳ ቪንቺ ኮድ፤ ገጽ 245***

  «ኢየሱስ ክርስቶስ መግደላዊት ማርያምን አግብቶ ሴት ልጅ ወልዷል:: የልጅቱም ስም ሣራ ይባል ነበር:: የኢየሱስ ክርስቶስና የመግደላዊት ማርያም ጋብቻ የታሪክ መዝገብ አንድ አካል ነው::» ***የዳ ቪንቺ ኮድ፤ ገጽ 254-249***

  «ኢየሱስ ክርስቶስ አይሁዳዊ ነበር:: በዚያም ዘመን የአይሁድ ማኅበራዊ ሕግ ወንድ ልጅ ሳያገባ እንዲኖር የሚፈቅድ አልነበረም:: እንደ አይሁድ ባሕል ለዐቅመ አዳም ከደረሱ በኋላ ለብቻ መኖር የተወገዘ ነበር:: የአይሁዳዊ አባትም ግዴታ ለወንድ ልጁ የምትሆነው ሚስት መፈለግ ነበር:: ኢየሱስ ክርስቶስ ባያገባ ኖሮ አንዱ ወንጌል እንኳን ይጠቅሰው ነበር::» ***የዳ ቪንቺ ኮድ፤ ገጽ 245***
- እንደ አይሁድ ባህል ሳያገቡ መኖር የተወገዘ አልነበረም:: ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው የመጀመሪያ መልእክቱ እንዲህ ብሏል:: «ላላገቡና ለመበለቶች ግን እላለሁ፤ እንደ እኔ ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው:: ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላል፤ ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ::» ***1ኛ ቆሮ 7:8 ::*** ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ራሱ «በስምንተኛው ቀን የተገረዝሁ ከእስራኤል ትውልድ ከብንያም ወገን ከዕብራውያን ዕብራዊ ነኝ::» ብሏል:: ይህም የዳን ብራውንን የግድ ማግባትን ሐሳብ ያፈርሰዋል:: ***ፊልጵስዮስ 3:5::***

# የዳቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 3

## የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መዋዕለ ሥጋዌ

- *ምንም ዓይነት ታሪካዊ መረጃ (የዓይን ምስክሮች ከሆኑት ከደቀመዛሙርቱም ጭምር) የኢየሱስ ክርስቶስንና የመግደላዊት ማርያምን «ጋብቻ» አያስረዱም:: የተጠቀሱት «የግኖስቲኮች ወንጌላትም» ራሳቸው ይኽንን አይገልጹም:: «የፊልጶስም ሆነ የመግደላዊት ማርያም ወንጌላት» ኢየሱስ ክርስቶስ ከመግደላዊት ማርያምም ሆነ ከሌላ «ሴት» ጋር የሚባለው ዓይነት ግንኙነት እንደ ነበረው አያስረዱም::*
- *ዳን ብራውን ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ይግባውና «አግብቷል» ማለት ተቀባይነት ያለው አካሄድ ነው ያለበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ አልገለጸልንም:: ይልቁኑ ተቀባይነት የሚኖረው አካሄድ በቅዱስ መጽሐፍ እንደ ተገለጸልን ከበርካታ ምክንያቶች አንጻር ጌታችን ፈጽሞ ያላገባ መሆኑን ማመናችን ነው::*
- *ጌታችን በሥጋ የመጣው ከቀድሞ ጀምሮ እንደ ተገለጸልን ለቤዛነት ሥራ ነው:: 12 ዓመት በሆነው ጊዜ እናቱ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርምና ጻድቁ ዮሴፍ ፈልገው በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ሲያገኙት «ከሦስት ቀንም በኋላ በመምህራን መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸው ሲጠይቃቸው በመቅደስ አገኙት፤ የሰሙትም ሁሉ በማስተዋሉና በመልሱ ተገረሙ::» **<u>ሉቃስ 2:46-49::</u>** ተብለናል::*
- *ጌታችንም በምድር በነበረ ዘመኑ ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሲሰብክ ቆይቷል:: የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራቹንም ቃል ለመስበክ ጃንደረባ ስለሆኑትም አስተምሯል:: «ይህ ነገር ለተሠጣቸው ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም፤ በእናቱ ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፤ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፤ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ፤ ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው አላቸው::» **<u>ማቴ 19:12::</u>***
- *ጌታችን በምድር ሳለ ራሱን እንኳን የሚያስጠጋበት ጐጆ አልነበረውም:: «ኢየሱስም ለቀበሮዎች ጉድጋድ ለሰማይ ወፎችም መስፈሪያ አላቸው፤ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም አለ::» **<u>ማቴዎስ 8:20::</u>** ታዲያ «ካገባ» የቤተሰቡ ቤት የት ነበረ? **<u>በማቴዎስ 12:47-50</u>** እንደ ተገለጸው ኢየሱስ ክርስቶስን ፍለጋ ከመጡት ቤተሰቦች ውስጥ «ሚስት» በማለት የተጠቀሰች እንደነበረች የሚያስረዳ ምንም ቃል የለም:: «እነሆ እናትህና ወንድሞችህ ሊያነጋግሩህ ፈልገው በውጭ ቆመዋል አለው፤ እርሱ ግን ለነገረው መልሶ እናቴ ማናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው? አለው:: እጁንም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘርግቶ እነሆ እናቴና ወንድሞቼ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ እህቴም እናቴም ነውና አለ::» **<u>ማቴ 12:47-50::</u>***

# የዳቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 3

***የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መዋዕለ ሥጋዌ***


- በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜም እናቱን ለሚወደው ደቀመዝሙር ለቅዱስ ዮሐንስ አደራ እንደ ሰጠ እንጂ «ሚስት» የተባለችው «ሴት» እንደሰጠ አናነብም:: ***ዮሐንስ 19:26-27::*** ካገባ «ሚስት» ተብላ ለተጠቀሰችውስ ከሞቱ በኋላ ጥበቃ እንዲደረግላት ማመቻቸት አልነበረበትምን?
- ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ ለመግደላዊት ማርያም የሰጣት ምላሽ ምንም ዓይነት «የጋብቻ» ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን ያመለክታል:: «ኢየሱስም ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ እኔ ወደ አባቴና ወደ አባቶችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላኮቻችሁም ዐርጋለሁ ብለሽ ንገሪያቸው አላት::» ***ዮሐንስ 20:17::*** ዳን ብራውን እንደሚለው ክብር ይግባውና «ከተጋቡ» በተጠቀሰው ቤታቸው እንዲገኛኙ ስለምን አልነገራትም?
- ቅዱስ ጳውሎስም ያገቡትን አንሥቶ በንጽጽር በተናገረበትም ክፍል ጌታችንን ጨምሮት አልተናገረም:: «እንደ ሌሎቹ ሐዋርያት እንደ ጌታ  ወንድሞች እንደ ኬፋም፤ እህት ሚስታቻችንን ይዘን ልንዞር መብት የለንምን?» ***1ኛ ቆሮንቶስ 9:5*** ጌታችን «ቢያገባ» ኖሮ ቅዱስ ጳውሎስ ጌታችንን ጨምሮ ለንጽጽር    ቢያቀርበው የበለጠ ጠንካራ ማስረጃ አይሆነውም ነበር?
- ብሉይም ሆነ ሐዲስ ኪዳን ጌታችን በሥጋ ፈቃድ የተገኘ ቤተሰባዊ የዘር ሐረግ እንደሌለው አስረግጠው ያስረዳሉ:: ***የሐዋርያት ሥራ 8:33*** ፤ ***ኢሳይያስ 53:8 ::*** ነቢዩ ዳንኤልም ጌታችን ለሞት ተሳልፎ በተሰጠ ጊዜ ኃጢአት የሌለበት ንጹሕ እንደሆነ የሚመሰክርለት የሥጋ ወገን እንዳልነበረው ተናግረዋል:: ***ትንቢተ ዳንኤል 9:26::*** ከሞቱ በኋላ ግን በሞቱ የገዛቸው፤ ያሸነፋቸውም መንፈሳውያን ወገኖች ነበሩት:: ***ኢሳያስ 53:10 ፤ 52:15::***
- በመንፈሳዊ አተረጓጎም ጌታችን የቤተክርስቲያን ሙሽራ ነው:: ***ካል ቆሮ 11:2*** የሐዲስ ኪዳን የትንቢት መጽሐፍም ይኸንኑ ይገልጽልናል:: ***ራእይ 19:9::***
- የትኞቹም የግኖስቲኮች ጽሑፎችም ሆኑ የዓይን ምስክርነት ሊሰጡ የሚችሉ ሌሎችም በዚህ መልክ የተገለጸውንና «በጌታችንና በመግደላዊት ማርያም መካከል ነበር» የሚባለውን የተለየ ግንኙነት አያስረዱም:: እነዚህ ሁለቱም «የመግደላዊት ማርያምና የፊልጶስ ወንጌላት» የግኖስቲኮች ወንጌል ስለነበሩ ከቅዱስ መጽሐፍ ቁጥር አልተቆጠሩም፤ የመቆጠርም ዕድል አላገኙም:: ግኖስቲኮች የሚባሉት ፈላስፎች «ለመዳን ከዚሁ ክፉ ከሆነው ቁሳዊ ዓለም በላይ የሆነውን ዕውቀት ማወቅ ያስፈልጋል» ይላሉ:: በ180 ዓ.ም. አካባቢ የነበሩ አንድ አባት «... እያንዳንዳቸው ግኖስቲኮች እንደ ችሎታቸው መጠን በየቀኑ አንድ አንድ አዳዲስ ነገር ይፈጥሩ ነበር፤ እንደዚህ ያለ የልብ ወለድ ፈጠራ የማያደርጉ ሁሉም ፍጹም ያልሆኑ ተደርገው ይቆጠሩ ነበር::» ብሏል::

# የዳቪንቺ ኮድ ወይስ? - ክፍል 3

***የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መዋዕለ ሥጋዌ***

- *የዳቪንቺ ኮድ «የመግደላዊት ማርያምን ወንጌል» «በመግደላዊት ማርያም የተነገረ ወንጌል» ይለዋል፡፡* ***ገጽ 247፡፡*** *እንደዚሁ ጽሑፉ «ጌታችንም ከሁሉ አብልጦ መግደላዊት ማርያምን ይወዳት ነበር ይላል፡፡»*
- *«የመግደላዊት ማርያም ወንጌል» የአጻጻፍ ዘይቤው ከ161-200 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ እንደ ተጻፈ ይጠቁማል፡፡ ይኸም መግደላዊት ማርያም ካረፈች ከረጅም ዓመታት በኋላ ማለት ነው፡፡*
- *«የፊልጶስ ወንጌል» መግደላዊት ማርያምን «የጌታችን ወዳጅ ነበረች፤ ያም ማለት ቢያንስ በአካል የመነካካት ዕድል ነበር» ይላል፡፡* ***የዳ ቪንቺ ኮድ፤ ገጽ 246***
- *ይኸ «የፊልጶስ ወንጌል» በመጀመሪያ የተጻፈው በኮፕት ቋንቋ ነው፤ ብራውን እንደሚለው በአራማይክ አይደለም፡፡ አንዳንድ ጸሐፍት « የፊልጶስ ወንጌል» በመጀመ ሪያ በግሪኮች ቋንቋ በጽርእ የተጻፈ ለማስመሰል ይሞክራሉ፡፡ ነገር ግን የዚሁ መጽሐፍ የአራማይክ ትርጉም የነበረበት ማስረጃ እስካሁን ድረስ በየትም አይገኝም፤ አልተገኘምም፡፡ በአራማይክ ቋንቋ የተፃፈም «የፊልጶስ ወንጌል» የለም፡፡*
- *በተጨማሪም በግሪክ ቋንቋ* (Koinonos) *ወዳጅ ወይም ባልንጀራ የሚባለው ወደ እንግሊዝኛው* Companion *እንደ ዳን ብራውን አባባል ቢወሰድ እንኳን የግሪክኛው* (Koinonos) *ጾታዊም ሆነ የጋብቻ ግንኙነትን የሚገልጽበት ምንም ጉን ወይም መንገድ የለውም፡፡*
- *ይህ ቃል በሐዲስ ኪዳን ዐሥር ጊዜ ተጽፎ ቢገኝም በአንድ ሥፍራም እንኳን ጾታዊ ወይም የጋብቻ ግኑኙነትን ጠቅሶ ወይም ገልጾ አናገኘውም፡፡* ***ማቴ 23:30፤ ሉቃስ 5:10፤ ቀዳ ቆሮ 10:18፤ ቀዳ ቆሮ 10:20፤ 2ኛ ቆሮ 1:7፤ 2ኛ ቆሮ 8:23፤ ፊልሞ 1:17፤ ዕብ 10:33፤ 1ኛ ጴጥ 5:1፤ 2ኛ ጴጥ 1:4፡፡***

# የዳቪንቺ ኮድ ወይስ...?




አዘጋጅ፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ነሐሴ 1998 ዓ.ም.

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org